በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ታህሳስ 2 ቀን 2013
አዲስ አበባ

# 92ኛ መደበኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 92ኛ መደበኛ ስብሰባ በሁለት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የልማት ዕቅድ ፍኖተ ብልጽግና 2013-2022 ሰነድ ላይ ነው፡፡ የልማት መሪ ዕቅዱ አገር በቀል የእድገት አቅጣጫን የተከተለ፣ በዘርፎች መካከል ሊኖር የሚገባው ትስስር የሚያጎለብት፣ የቀጣይ አስር ዓመታት የሚተኮርባቸውን የልማት ምሰሶዎች እና የትኩረት መስኮች በሚገባ የለየ፣ የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ፣ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ የሚያስችል ብሎም የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን ለማድረግ እና የአፍሪካ ብልጽግና ተምሳሌት እንድትሆን የሚስችል እቅድ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በልማት ዕቅድ ፍኖተ ብልጽግና 2013-2022 ሰነድ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል አጽድቆ ስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የመገናኛ ብዙሃን ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ የዜጎችን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት የሚያረጋግጠጥ፣ የመገናኛ ብዙሃን በተቋምነታቸው የአሰራር ነፃነት እንዲኖራቸው እና የሃሳብ ብዝሃነትን የማስተናገድ አቅም እንዲያጎብቱ የሚስችል፡ ሁሉንም አይነት የሚዲያ ዘርፎች በወጥነት በአንድ የህግ ማእቀፍ ማስተዳደርና መቆጣጠር የሚያስችል፣ የቴክኖሎጂ እድገት የደረሰበትን የሚዲያና ብሮድካስት ቴክኖሎጂ እውቅና የሚሰጥ፣ በገለልተኝነት ዘርፉን የሚመራ ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነ ተቋማዊ ስርዓት ማጎልበት የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

//